# ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኤክስፕረስ  4/7/2021: አዲስ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኮቪድ-19 ሰሌዳ (ዳሽ ቦርድ) እና መጪው የኮሚዩኒቲ ስብሰባ

***የዚህ ሳምንት ዋና ርእሶች፤***

- የትምህርት ቤት ቦርዱ የት/ ቤት ስም በተመለከተ የመጨረሻው ውሳኔ ሲያሳልፍ ይመልከቱ።
- አዲስ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኮቪድ-19 ሰሌዳ (ዳሽ ቦርድ)
- የአካላዊ ርቀት መመሪያዋች በእኛ ት/ቤቶች
- በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የቦርድ አባላትና የኮሚዩኒቲ መሪዋች ስብሰባ  ስለድብልቅ የትምህርት ፕሮግራም ለሚነሱ ጥያቄዋች መልስ ለመስጠት እና ስለበጋውና የፎል ወቅት  ትምህርት በሚደረግ ገለፃ  ተሳታፊ ይሁኑ።
- የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ኮቪድ-19 የስብሰባ አዳራሽ ውይይት ኤፕሪል 13-14
- $40,000 የነፃ ትምህርት እድል አሸናፉ ተገለፀ።
- የቲይታን ቫርሲቲ ፉትቦል የዲስትሪክት ውድድር!
- በC-SPAN የትረካ ፊልም ውድድር ስማቸው በክብር የተጠሩ ተማሪዋች
- ሁለት የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. መሪዋች እውቅና ተሰጣቸው።
- ለተማሪዋች የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ።

---

የተከበራችሁ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ  ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባላት፤

 እኔ እንደምገምተው አስደሳች እና ጤናማ ከነበረው የስፐሪንግ የእረፍት ግዜ ሁላችንሁንም በቅድሚያ እንኳን በደህና መጣችሁ እላለሁ።   ሁላችሁም ትንሽ ዘና ባላችሁ በዚህ ሳምንት ወደ ስራ መመለስ ዝግጁ እንደሆናችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ታሪክ ይህ ትልቅ ሳምንት ነው።  ነገ ምሽት የኤሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ  ለሁለቱም ትምህርት ቤቶች ፤ ቲ.ሲ.ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ማቲው ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ ስም ማውጣት ላይ ውሳኔ ያሳልፋል። .

 ይህም  ለሁሉም ተማሪዋችና ሰራተኞች ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ በምናደርገው ስራ እንቅስቃሴ ሂደት አዲስ ዘመን በእኛ ትምህርት አስተዳደር  መጀመሩን ያሳያል። እናም  የእኛን ምንነት የሚያከብር እና ማንነት የሚያንፀባርቅ እና የወደፊት ህይወታችን አቅጣጫ የሚያመለከት  የእኛ መልካም የትምህርት ከባቢ ሁኔታ እንፈጥራለን ። ሁላችሁንም ግዚያችሁን ወስዳችሁ በዚህ ጠቃሚ ሂደት በመሳተፋችሁ ለማመስገን እወዳለሁ።

በዚህ ሳምንት በተጨማሪ በትምህርት ቤት አስተዳደራችን  የሚያገለልግሉ ዋና የስራ ኋላፊዋችን ለማክበር እንፈልጋለን።  በብሄራዊ ረዳት ርእሰ መምህር ሳምንት ለትምህርት ቤታችን እና ለተማሪዋች፣ ለቤተሰቦችና ለሰራተኞች ትልቅ አስተዋፃ ያደረጉ ምክትል ርእሰ መምህራኖችን ለማመስገን በተዘጋጀው ከእኔ ጋር እንዲሆኑ ለመጠየቅ እወዳለሁ ።

ከዚህ በተጨማሪ  በት/ቤቶች የአካል ርቀት በተመለከተ የተዘጋጀውን  አዲሱን  የCDC መመሪያ  በክፍል ውስጥ በተማሪዋች መካከል ያለው የርቀት መጠን  አስተማመኝ የአየር ስርጭት አገልግሎት በክፍል ውስጥ እስካለ ድረስ ከስድስት ወደ ሶስት ፊት ዝቅ ማድረግ እንደሚችል ገልፃል።  በአሁኑ ግዜ  የስድስት ፊት ርቀት የአካላዊ ርቀት በስራ ላይ የዋለ ሲሆን እና  አዲሱ መመሪያ ምን ያህል በስራ ሊውል እንደሚችል እና በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ላይ የሚያመጣውን ለውጥ በመመልከት ላይ ነን ። ይህም ማለት በድብልቅ የትምህርት ፕሮግራም በዙ ተማሪዋች መጨመር እንችላለን ማለት ነው።     በተደጋጋሚ በሚቀርቡ ጥያቄዋች  የአካላዊ ርቀት በሚመለከት ፣ እድሀ መረጃ ለማግኘት ዝርዝሩን ከታች ይመልከቱ።

እባካችሁ እራሳችሁን፣ ጤንነታችሁን ጠብቁ እና ተሳታፊ ይሁኑ።

ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ ( Gregory C. Hutchings, Jr).
ሱፐር ኢንቴንደንት

## የትምህርት ቤት ቦርዱ የት/ቤት ስም በተመለከተ የመጨረሻው ውሳኔ ሲያሳልፍ ይመልከቱ።




ነገ ምሽት የኤሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ  ለሁለቱም ትምህርት ቤቶች ፤   ቲ.ሲ.ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ማቲው ማውሪ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ ስም ማውጣት ነገ  ሐሙስ ፣ ኤፕሪል 8 ቀን በ5.00 ምሽት ላይ ውሳኔ ያሳልፋል። የቦርዱ ስብሰባ  በኦንላይ ይታያል ፤ viewed live online እና  ACPS-TV በከተማው ቴሌቭዠን ቻናል  71 ይቀርባል።

ይህ ታሪካዊ ውሳኔ ድምፅ አጠቃላይ ሂደት ተማሪዎችን፣ አስተማሪዋን ሰራተኞችና የቀድሞ ተማሪዎች እና ህብረተሰቡን ያሳተፈ ነበር። ስያሜው  The Identity Project በመባል ይታወቃል።

አዲስ ስም ለመለወጥ የሚያጠይቀው ወጪ መጠን ግምት በቲ.ሲ. ዊሊያም እስከ $325,000 እንዲሁም በማቲው ማውሪ ደግሞ $5,000  ነው። ትምህርት ቤቶች በአዲስ ስም ከጁላይ 1፣ 2021 ጀምሮ ይጠራሉ።

## አዲስ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኮቪድ-19 ሰሌዳ (ዳሽ ቦርድ)

የእርስዎ እና የሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ጤንነት ማረጋገጥ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን ማረጋገጥ እንፈልጋለን። አዲስ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ኮቪድ-19 ሰሌዳ (ዳሽ ቦርድ) የሚ ጋጥሙ ጉዳዩችን ከማርች 1፣ 2021 ጀምሮ ያሳያል እና በየሳምንቱ ሰኞ ከሰዓት በኋላ 4.00 ላይ ወቅታዊ መረጃ እንዲይዝ ይደረጋል።

**View the ACPS COVID-19 Dashboard**

በአሌክሳንደሪያ ከተማ ስላለው ስለ ኮቪድ-19 መረጃ እና ጥያቄ  የኮቪድ -19 የነፃ ምርመራ ቦታ ጭምር ለማወቅ እባክዎን ይህን ይመልከቱ፤ Alexandria Health Department COVID-19 website. እንደአመቺነቱ መጠቀም የሚቻል የሰባት ቀናት የኮቪድ መያዝ የሚያሳይ መረጃ የCOVID-19 የሚመለከቱ ጉዳዮች እና የየቀኑ እና በአጠቃላይ በድምሩ የሚታዪ ነገሮችን እንዲሁም በህመሙ ምክንያት በአሌክሳንደሪያ የሞቱ ሰዋች መረጃ በከተማው ድረገፅ ማየት  ይቻላል።City of Alexandria website. የCDC የK-12 ትምህርት ቤቶች መረጃ መስፈርት በሚከተለው ድረገፅ ማየት ይችላል፤  Virginia Department of Health website.

## የአካላዊ ርቀት መመሪያዎች በእኛ ት/ቤቶች ውስጥ

በቅርብ ግዜ ከበሽታዎች መከላከያ እና መቆጣጠሪ ማእከል (CDC) የወጣው እንደሚያሳየው ማስክ በማድረግ፣ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቢያንስ ሶስት ፊት ርቀት በመካከላቸው መጠበቅ ይችላሉ ። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ጋር በጋራ የጤንነት መጠበቂያ እርምጃዎችን በት/ቤቶቻችን ወስዶል፤ የፅሁፍ ምልቶችን በማዘጋጀት እና አሰራሮችን በመጠቀም አካላዊ ርቀት እንዲከበሩ ለማድረግ ጥረት አድርጓል። አካላዊ ርቀት መጠበቅ አንድኛው የመከላከያ እርምጃ ነው።

**የህዝብ ጤንነት አጠባበቅ መመሪያ መሰረት እና ከአሰራር ሂደት አኳያ በዚህ ግዜ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የስድስት ፊት ርቀት እስከ ዓመት መጨረሻ ድረስ በስራ ያውላል።** **[Learn more in our FAQs](#).**

አዱሱን መመሪያ በምናጠናበት እና ለ2021 በጋ ወቅት እና ለፎል ወቅት ለሶስት ፊት ርቀት በስራ ለማዋል አስፈላጊውን ዝግጅት በምናድርግበት ወቅት ተጨማሪ መረጃዎችን ለቤተሰቦች እንዲያውቁት ይደረጋል።

## በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የቦርድ አባላትና የኮሚዩኒቲ መሪዎች ስብሰባ ስለድብልቅ የትምህርት ፕሮግራም ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እና ስለበጋውና የፎል ወቅት ትምህርት በሚደረግ ገለፃ ተሳታፊ ይሁኑ።

ጥያቄዎች እንዳላችሁ እናውቃለን እናም የቨርችዋል ቦታ አዘጋጅተናል ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሱፐር ኢንቴንደንት ዶ/ር ሐትቺንግስ ( Dr. Hutchings) ፤ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር፣ እና ሁለት የትምህርት ቤቱ ቦርድ አባላት አፈላጊ ወቅታዊ በሆኑ እኛ ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ቤተሰቦች ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመስማት ለወላጆችና ለተማሪዎች ለስራተኞች ስብሰባ የመረጃ ልውውጥ ይኖራል።

ዶ/ር ሐትቺንግስ ( Dr. Hutchings ስለድብልቅ የትምህርት ፕሮግራም እና የበጋ ትምህርት እና ለ 2021-22 የትምህርት ዘመን የእቅድ ዝግጅት ) ወቅታዊ መረጃ ያቀርባሉ። ከአጭር ገለፃ በሆላ የኮሚዮኒቲ አባላት ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ ይጋበዛሉ በዙም አማካኝነት እና ፓናል አባላት የተቻለውን ያህል መልስ ይሰጣሉ።

**ለቤተሰቦች ስብሰባ**

- ሰኞ ፡ኤፐሪል 19 ቀን ከምሽቱ5.30 -6፡30 ሰዓት [ከእኛ ጋር በዙም ይገናኙ፤](#)
- ሐሙስ ፡ኤፐሪል 22 ቀን ከእኩለ ቀን - 7.00 ሰዓት ከእኛ ጋር በዙም ይገናኙ፤ [Join us on Zoom](#)
- ሰኞ ፡ኤፐሪል 19 ቀን ሰዓት በኋላ 3.30 -4.30 ሰዓት ከእኛ ጋር በዙም ይገናኙ፤ [Join us on Zoom](#)

ስፓኒሽ፣ አማርኛ እና አረብኛ አስተርጎሚዎች በየስብሰባው ይገኛሉ። በስብሰባው እንደሚገኙ ተስፋ እናደርጋለን!

## የአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ኮቪድ-19 የስብሰባ ውይይት ኤፐሪል 13-14

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ጋር በመተባበር ሁለት የአዳራሽ ስብሰባ አዘጋጅቶል ማክሰኞ ከእኩለ ቀን እስከ 1.00 ከሰዓት በሆላ ድረስ እና አሮብ ኤፐሪል 14 ከምሽት 5.30 እስከ 7.00 ድረስ የኮቪድ 19 መያዝ መረጃ ሲደርስ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ መረጃዎችን ይሰጣሉ። እንዲሁም ስለCDC እና የቨርጅኒያ ጤና ዲፓርትሜንት ለት/ቤቶ ስላዘጋጁት የተሻሻሉ መመሪያዎችና ሰዎች የት ክትባት መውሰድ እንደሚችሉ መረጃ ይሰጣሉ።

AHD ኮቪድ -19 ስብሰባ ውይይት ፤

- ማክሰኞ ፣ ኤፕሪል 13 ቀን ከእኩለ ቀን እስከ 1.00 ከሰዓት ከእኛ ጋር በዙም ይገናኙ፤ Join us on Zoom
- እሮብ ፤ኤፕሪል 14 ቀን ከምሽቱ5.30- 7.00 ሰዓት ከእኛ ጋር በዙም ይገናኙ፤ Join us on Zoom

ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ጥያቄያቸውን በቅድሚያ ለስብሰባ ከመጀመሩ በፊት እንዲያቀርቡ ይጠያቃሉ። Submit your questions online.

የትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

## $40,000 የቲይታን የነፃ ትምህርት እድል አሸናፊ ተገለፀ።




የአሌክሳንደሪያ ስኮላርሽፕ ፈንድ (Scholarship Fund of Alexandria) (SFA) አስደሳች ዜና ለቲ.ሲ. ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለዘንድሮ ተመራቂ ሳራ አባስ ( Sara Abbas ) የ40.000 ትልቁን የነፃ ትምህርት እድል "Titans in Tech" ሰጥቶል ። የቲይታን (The Titans in Tech Scholarship) የተመሰረተው በዚህ ዓመት ነው በቲ.ሲ ዊሊያም የቀድሞ ተማሪ እና የ Brett Sirois, መስራች እና ዋና አስቀጣሪ የሆነው የ Stem IT, የቲ.ሲ ዊሊያም ተማሪዎች የአራት ዓመት የኮምፒወተር ሳይንስ የኮሌጅ ትምህርት በቨርጅኒያ ዩኒቨርስቲዎች መከታተል እንዲችሉ በማገዝ Learn more about this incredible honor.

# የቲይታን ቫርሲቲ ፉትቦል የዲስትሪክት ውድድር!




የቲይታን ቫርሲቲ ፉትቦል የዲስትሪክት ቡድን የ Gunston District Championship ውድድር በ20 ዓመታት ግዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ መደረስ ችሎል።

በመጀመሪያ ዓመት ዋና እሰልጣኝ Rodney Hughey መሪነት የቲይታን ሁሉም አስቸጋሪ ሁኔታዋች በማለፍ ሁሉም ውድድሮች በመጨዋት ሳይሸነፉ (4.0) በማግኘት በዲስትሪክቱ እና በእጠቃላይ 4-2 አግኝተዋል። ይህ ከ1990 ወዲህ ቡድኑ የዲስትሪክት ዋንጫ ለመጀመሪያ ግዜ ነው የተገኘው።

የቲይታን Quarterback Chacai Campbell በ ዲስትሪክቱ የእመቱ ምርጭ ተጨዋቾች እንዲሁም አሰልጣኝ Hughey የዓመቱ ምርጥ አሰልጣኝ ክብር በማግኘታቸው እንኳን ደስ አለህ ማለት እንፈልጋለን።

## በC-SPAN የትረካ ፊልም ውድድር ስማቸው በክብር የተጠሩ ተማሪዎች




እንኳን ደስ አለቸው ለቲ.ሲ. ዊሊያም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ይአ10ኛ ክፍል ተማሪዎች፤ Helen Russell, Alison Avelar እና Elena Gutierrez በC-SPAN በC-SPAN 2021 S2021 StudentCam Documentary ውድድር በክብር ተሳታፊነት በመሸለማቸው። C-SPAN ከ2300 በላይ ተማሪዎችን የተዘጋጀ ፊልም ከ43 ስቴትና ከዲ.ሲ. እና ከሲንጋፖርና ከፓኪስታን ጭምር ደርሶታል። ተማሪዎቹ ከአምስት እስከ ስድስት ደቂቃ የሚሆን ፊልም ፕሬዘደንቱና ኮንግረስ ሊመለከቱት ስለሚገባ ጉዳይ እንዲያዘጋጁ ተጠይቀው ነበር። ከብዙ ማጣራት በኋላ እና በበርካታ ዳኞች ከታየ በኋላ C-SPAN የዚህን ዓመት አሸናፊ አሳውቋል፤ [150 prize-winning documentaries].

የቲ.ሲ ዊሊያም ቡድን የራሳቸውን የትራካ ፊልም በመፃፍ አዘጋጅተው በመቅረፅ ስራ አከናውነዋል። ["Dear Mr. President: History, or Progress?"] የቲ.ሲ ዊሊያም ቡድን እንደ ክብር ስም የተገለፅ ሲሆን $250 ሽልማት አግኝተዋል። እነዚህ ተማሪዎች Vilma Zefran አስተማሪነት የቴሌቪዝንና ሚዲያ ዝግጅት ክፍልተማሪዎች ናቸው።

አመታዊ የStudentCam ውድድር አዘጋጅ C-SPAN Education Foundation ነው። ቪዲዮ በትምህርት ባለሞያዎችባ በ C-SPAN ተወካይ በቀረበው ርእስ በሚመለከት በትክክል ገላጭ የሆነ ፊልም መዘጋጀቱን የተገመገመ ሲሆን ጥራቱ እና ርእሱ የተገለፀበት መንገዶች እና የሲ C-SPAN የፕርግራም ዝግጅት የሚያሳይ መሆኑ ተገምግሞል።

## ሁለት የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. መሪዎች እውቅና ተሰጣቸው።

ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሱፐር ኢንቴንደንት ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr.) እና ለሳሙኤል ተከር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህር Rene Pascha እንኳን ደስ አላችሁ። በ Virginia Association of Elementary Principals (VAESP) ለሁለቱ የአመራር ብቃት ሽልማት ተሰጥቶቸዋል። በ2021 VAESP ዓመታዊ ስብሰባ ወቅት በጁን ወር ስማቸው ይጠቀሳል።

Dr. Hutchings [Pathfinder Award] በዘር ፍትሃዊነት፤ በተመለከተ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በሰጡት አመራር መሰረት የ2021 ሽልማት ተቀባይነት ተመርጠዋል ። “The Pathfinder በቨርጅኒያ በትምህርት አመራርና በአንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት

ቅልቅ አስተዋፃ ላደረጉ በተግባር የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሻሽል ጥረት ላደረጉ ሽልማት የ VAESP አባል ለሆኑም ሆኑ ላልሆኑትም እውቅና ይሰጣል። በየዓመቱ የሚሰጠው አንድ ሽልማት ብቻ ነው።

Rene Paschal የVAESP's The School Bell Awardሽልማት ከተቀባዩች መካከል አንዱ ናቸው። Paschal እውቅና የተሰጣቸው የተሻሻለ የትምህርት ግዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት እና የተለያየ የህብረሰተብ ፍላጎቶችን በማሞላት ለሰሩት ስራ ነው። "The School Bell ሽልማት ለትምህርት ቤት ለሚሰሩ አመራሮች የሚሰጥ ሲሆን የ VAESP አባል የሆኑ እና ለት/ቤታቸው ለትምህርት አመራር፣ ለስትቴት ማህበር እና ለብሄራዊ ማህበሩ እና ለሌላ የትምህርት ድርጅቶች ቅልቅ አስተዋፆ ላደረጉ የአመራር አባላት የሚሰጥ ነው። ሽልማቱ የሚሰጥ እጩው ባደረጉት አስተዋፆ መሰረት እና የስራ ልምዳቸው በማየት ነው ያገኙነት ሽልማት፣ የፓለቲካ እንቅስቃሴ፣ የድርጅት እና የማህበር ተሳትፎ በመመለከት ነው የሚካሄደው።

## ለተማሪዋች የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ።

የእይንና የመስማት ምርመራ በዚህ ወር ይጀመራል። የቨርጅኒያ ህግ መሰረት የ Section 22.1-273 ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ለተማሪዋች የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ በማዋእለ ህፃናት እና በሶስተኛ፣ በሰባተኛ እና አስረኛ ክፍል ላሉ ተማሪዋች እንዲሁም ለማንኛውን አዲስ ለሆነ ተማሪ ማድረግ ይኖርበታል።

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ለተማሪዋች የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ በድብልቅ የትምህርት ፕሮግራም ለሚከታተሉ ተማሪዋች በኤፕሪል 13 ትምህርት ሲጀመር የጤና አሰራሩን በመከተል ማካሄድ ይጀምራል። የማራቱ ምርመራ ስራ በትምህርት ቀናት ይካሄዳል ከ20-30 ዱቂቃዋች ሊወስድ ይችላል።

በመዋእለ ህጻናት ፣በሶስተኛ ክፍል በሰባተኛ እና አስረኛ ክፍል ላሉ ተማሪዋች እንዲሁም ለማንኛውን አዲስ ለሆነ ተማሪዋች ሙሉ በሙሉ በቨርችዋል ትምህርት የሚማሩ በዚህ ምርመር እንዴት ሊሳተፉ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃዎች በኢሜል ሊደርሳቸው ይደረጋል።

ተጨማሪ መረጃ ስለ የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ በዚህ ድረገፅ ሊያገኙ ይችላሉ፡ ACPS Screenings ስለ የመስማትና የአይን ማጣሪያ ምርመራ ጥያቄዋች ያሎቸው ቤተሰቦች በሚከተለው ከትምህርት ቤት ነርስ፤ ጋር መገናኘት ይችላሉ፤ school nurse.

## የምግብ አቅርቦት

ለሁሉም የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዋችና እድሚያቸው ከሁለት አመት በላይ ለሆኑ ልጆች የሚያገለግሉ.ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በርካታ የማከፋፈያ ቦታዋች በመላው አሌክሳንደሪያ ከተማ አሉ፤ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የምግብ ማከፋፈያ ቦታዋች እና ጊዜ ለመመልከት ይህን ይመልከቱ፤ .

## ከአሌክሳንደሪያ ጤና ዲፓርሜንት ወቅታዊ መረጃ

ወቅታዊ መረጃ ይህን ይመልከቱ፤ www.alexandriava.gov/Coronavirus.

## የጤና ጉዳይ ማሳሰቢያዋች

**ጤንነት አይሰማዎትም?**

ከቤተሰብ ሀኪም ጋር ይገናኙ፤ ምንም የጤና ኢንሹራንስ የለዎትም? ከኔበርሁድ ሄልዝ(Neighborhood Health) ጋር  በስልክ ይገናኙ 703-535-5568.

---

ጥያቄዎች፣ አሳሳቢ ጉዳይ ወይም አስተያየት ? [ከእኛ ጋር ይገናኙ፤](#).